## ለየካቲት ፲፪ ሰማዕታት መታሰቢያ

## (፲፱፻፳፱ ዓ.ም. — ፳፻፲፪ ዓ.ም.)

የኢትዮጵያን ስም እየጠራሁ ኢትዮጵያዊ ነኝ የምለው
ክቡር ሰንደቅ ዓላማዬን በሙሉ ልብ የማሳየው
የነፃነት ዓርማ የሆነች
በእምነቷ፣ በታሪኳ፣ በጽናቷ የገነነች
በልጆቿ ደም እና አጥንት ማንነቷን ያስከበረች
መላ አፍሪካን ያሰደነቀች
ኃያላኑን ያስገበረች
እናት አገር አለኝ እያልኩ በዚያች ምድር የምኰራው
ታላቅ ስሟ፣ ውብ ቋንቋዋ በዙሪያዬ የሚያበራው . . .
ብዙ ሕይወት፣ ብዙ ዋጋ በአንደበት የማይገልጹት
ብዙ ስቃይ፣ ብዙ ትግል በመለኪያ የማይሰፍሩት
ተከፍሎ ነው በዜጎቿ በንጹሓን መስዋዕትነት
ሊሞቱላት በቆረጡ በጀግኖቿ ሰማዕትነት
የአረመኔ፣ የፋሽስትን የጭካኔ ጭፍጨፋውን
የመርዝ ጋዝ፣ የመትረየስ፣ የእሳት ንዳድ፣ የአካፋውን
በከተማ፣ በገዳማት ወራሪው ጦር የፈጀውን
የደረሰው የግፍ እልቂት ዓለም ያየው የሚያውቀውን . . .
አንረሳውም ወገኖቼ በእናንተ ነው መኖራችን
አገራዊ ኲራታችን፣ ኢትዮጵያዊ ውበታችን
ከምድሪቱ ተዋሕዶ ዕጣ፣ ኑሮ፣ ሕይወታችሁ
ለነፃነት፣ ለአንድነቷ፣ ለማተቧ ተሰዋችሁ . . .
አትረሳችሁም ኢትዮጵያ ታሪካችሁ ይነገራል
በትውልዶች ይታሰባል፣ ይታወሳል፣ ይዘከራል
አደራ እናንተም  እንዳትረሷት
ምድራችሁን አይዞሽ በሏት. . .
ከሰማይ ቤት፣ ከገነት ደጅ ትችሉ እንደሁ ልታግዟት
ፀጋ፣ ክብሯ እንዲመለስ ለኢትዮጵያ ጸልዩላት።

---

ቴዎድሮስ አበበ
Washington, DC